ቁጥር- አ1162/11/15421

ቀን 05 2017

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ለህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ( ህወሓት)

<u>መቐለ</u>

**<u>ጉዳዩ፦ ፓርቲው ከፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መታገዱን ስለማሳወቅ፤</u>**

የኢትዮጵያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ያሻሻለውን አዋጅ ቁጥር 1332/2016 መውጣቱን ተከትሎ ህወሓት ለቦርዱ ሐምሌ 19 ቀን 2016ዓም በቁጥር 3944/ማከ1/644 በፃፈውና ከዚሁ ደብዳቤ ጋር አያይዞ ባቀረበው ዝርዝር ሰነዶች እንዲሁም የኢፌድሪ የፍትህ ሚኒስቴር ሰኔ 17 ቀን 2016ዓም በቁጥር ፍሚ1/1345 በፃፈው ደብዳቤ መነሻነት ቦርዱ ጉዳዩን መርምሮ ለህወሓት የክልላዊ ፓርቲ በልዩ ሁኔታ የምዝገባና የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ነሀሴ 3 ቀን 2016ዓም መስጠቱና ፓርቲውም ይህንኑ ሰርትፊኬት ከቦርዱ መቀበሉ ይታወቃል።

ቦርዱ ይህንኑ በልዩ ሁኔታ የምዝገባና የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለፓርቲው ሲሰጥ በህጉ መሰረት ፓርቲው ሊከተለውና ሊፈፅመው ስለሚገባው ህጋዊ ግዴታዎች ነሀሴ 3 ቀን 2016ዓም በቁጥር አ1162/11/15180 በተፃፈ ደብዳቤ ገልጿል። በተጨማሪም የአዋጅ ቁጥር 1332/2016ዓም ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 25/2016ዓም አውጥቶ በስራ ላይ አውሏል።

ፓርቲው በአዋጁና በመመሪያው ከተጣለበት ኃላፊነትና ግዴታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ በልዩ ሁኔታ ከተመዘገበበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የቦርዱ ታዛቢዎች በተገኙበት ጠቅላላ ጉባኤ ማድረግ ፣በዚህም ጉባኤ በአዋጁ መሰረት ያቀረበቸውን ሰነዶች ከአዋጁ ጋር በማጣጣም ማፅደቅና አመራሮቹን ማስመረጥ ናቸው። በሌላ በኩል የቅድመ ጉባኤውን ዝግጅት የተመለከቱ ስራዎችን ቦርዱ መከታተል እንዲችል ፓርቲው ጠቅላላ



ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe
ትዊተር
@NEBEthiopia
ኢሜይል
contact@nebe.org.et
ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለከተማ
ፊሰቶሬንት ፕላ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ጉባኤውን ከማድረጉ 21 ቀናት በፊት የጉባኤውን ቀን ለቦርዱ እንዲያሳውቅ ቦርዱ ለፓርቲው ማስታወቁ ይታወሳል።

ፓርቲው በአዋጁና  በመመሪያው መሰረት ያለበትን ግዴታ እንዲወጣ ቦርዱ በተለያየ ጊዜ ይህውም ነሀሴ 6ቀን 2016ዓም በቁጥር አ1162/11/15181 ፤ነሀሴ 15 ቀን በቁጥር አ1162/11/15199 ፤ነሀሴ 20 ቀን 2016ዓም በቁጥር አ1162/11/15209፣ ጥቅምት 21 ቀን 2017ዓም በቁጥር አ1162/11/15278 በተፃፉ ደብዳቤዎች ያሳሰበና ያስታወቀ ሲሆን ፤ በመጨረሻም ታህሳስ 17 ቀን 2017ዓም በቁጥር አ1162/11/15349 በተፃፈ ደብዳቤ ጠቅላላ ጉባኤ የማድረጊያ ጊዜ ገደቡ ሊጠናቀቅ ከሁለት ወር ያነሰ ጊዜ እንደቀረው በመግለፅ ፓርቲው በህግ የተጣለበትን ግዴታ እንዲፈፅም በማሳሰብ ፓርቲው ይህንን የህግ ግዴታ በወቅቱ ሳይፈፅም ቢቀር ቦርዱ ህጉን መሰረት በማድረግ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን አስታውቋል።

ይሁንና ፓርቲው የአዋጁንና የመመሪያውን ደንጋጌዎች እንዲሁም የቦርዱን ውሳኔዎች በማክበር የጠቅላላ ጉባኤ ሳያካሄድ፣ መተዳደሪያ ደንቡንና ፕሮግራሙን ሳያፀድቅና አመራሮቹን ሳይመርጥ በህግ የተሰጠው የስድስት ወር ጊዜ ተጠናቅቋል።

ህወሓትም በልዩ ሁኔታ ተመዝግቦ እንደሚንቀሳቀስ ፓርቲ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ህግ፣ መመሪያና ውሳኔዎችን አክብሮ መንቀሳቀስ ሲገባው በአዋጅ ቁጥር 1332/2016 አንቀፅ 3(11) (ሀ) እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ አንቀፅ 16(6) የተደነገገውን ጥሶ ተገኝቷል።

በዚህ መሰረት ቦርዱ የካቲት 4 ቀን 2017ዓም ባደረገው ስብሰባ ጉዳዩን ምርምሮ ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቷል፤

1. ፓርቲው ከፍ ብሎ የተጠቀሱት አዋጅና መመሪያ ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ባለማክበር  ጉልህ ጥሰት በመፈፀሙ አዋጅ ቁጥር 1332/2016ን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያው ቁጥር 25/2016 አንቀፅ 18(1) መሰረት ፓርቲው ይህ ውሳኔ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ለሶስት ወራት በምንም አይነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይሳተፍ እንዲታገድ ቦርዱ ወስኗል።

2. ፓርቲው ለእግዱ ምክንያት የሆነውን ጥሰት በማረም፤ አዋጁን ፤አዋጁን ተከትሎ የወጣውን መመሪያ፣ የቦርዱን ውሳኔዎችና ትዕዛዞች በማክበር ፓርቲው ሊያደርግ የሚገባውን ጠቅላላ ጉባኤ ለማድረግ የሚያስችለውን የጉባኤ ቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ለመስራት ለቦርዱ በፅሁፍ ሲያሳውቅና ቦርዱ ይህንኑ ሲያረጋግጥ በመመሪያው አንቀፅ 18(2) መሰረት ዕግዱን የሚያነሳ መሆኑን ቦርዱ ወስኗል።
3. ይሁንና ከፍ ብሎ ለፓርቲው በተሰጠው የሶስት ወራት የዕግድ ጊዜ ፓርቲው የእርምት ዕርምጃ ሳይወስድ ቢቀር በአዋጅ ቁጥር 1332/2016 አንቀፅ 3(11) (ሐ) እና በመመሪያ ቁጥር 25/2016 አንቀፅ 19( 1) (ሐ) መሰረት ቦርዱ የተለየ አካሄድ ሳይከተል የፓርቲው ምዝገባ እንዲሰረዝ ቦርዱ የወሰነ መሆኑን በአክበሮት እንገልፃለን።

ከሰላምታ ጋር

ሜላትወርቅ ኃይሉ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ